# አንድነት፣ ብርቱካንና ምርጫ

መስፍን ወልደ ማርያም

ጳጉሜን 2001

አንድነት ለዴሞክራሲና ፍትሕ ፓርቲ ሦስት ጉልህ የሆኑ ችግሮች ተጋርጠውበታል፤ አንደኛ የፓርቲው መሪ የወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ መታሰር፣ ሁለተኛ በፓርቲው ውስጥ በአባሎችና በአመራሩ መሀከል የተፈጠረው አለመግባባት እየከረረ መሄድ፣ ሦስተኛ ያለምንም ዝግጅት የምርጫው መቃረብ ናቸው፤ ምናልባትም አራተኛ ችግር ሊባል የሚቻለው ከላይ ከአንድ እስከሦስት የተዘረዘሩት ችግሮች ቅደም-ተከተል ነው።

በመሠረቱ የወይዘሮ ብርቱካን መታሰር የፓርቲው ችግር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የፖሊቲካ ፓርቲዎችና በሰላማዊ የፖሊቲካ ትግል ለሚያምነውና አገሩ በዚያ ትግል ውስጥ ገብታ ሥልጣንን ለመግራት የሚቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር ለማየት የሚናፍቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ችግር ነው፤ ፍርጥ አድርጎ እውነቱን ለመናገር የወይዘሮ ብርቱካን መታሰር የኢትዮጵያ ሕዝብ መታሰር ነው፤ የነጻነት፣ የፍትሕና የሕጋዊነት፣ የእኩልነት፣ የዴሞክራሲ ሥርዓትና የፖሊቲካ ምርጫ መታሰር ነው፤ በኢትዮጵያ የሥልጣን ፉክክር ውስጥ ወጣቶችንና ሴቶችን አስወግዶ ተስፋቸውን ማሰር ነው፤ ይህ ሁሉ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያሳድረው መከፋት ለማንም የፖሊቲካ ፓርቲ አይበጅም፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማናቸውም ዓይነት እድገት አይበጅም፤ በሰላም ላይ ለተመሠረተ ውይይትና መግባባት አይበጅም፤ የ97ን ቁስል በእንጨት መጎርጎር ጡንቻን እንጂ ሕጋዊነትን ስለማያረጋግጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ የሚያዋርድና ትዝብት ውስጥ የሚጨምር ነው።

ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ከታሰረች ወዲህ በፓርቲው ውስጥ በተፈጠረው ወሰንና ይሉኝታ በሌለበት የሥልጣን ጥም አንድነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት፣ ለነጻነቱና ለእኩልነቱ፣ ለሕጋዊ ሥርዓትና ለእድገቱ የተለመውን ስንቅ ሁሉ ድራሹን የሚያጠፋና በገሀድ የሚታይ የውንብድና ተግባር እየተፈጸመ ነው፤ እነዚህን ተግባሮች በከፊል ‹‹ዝምአንልም›› ብለው የተነሡት የፓርቲው አባሎች በተለያዩ መንገዶች ለሕዝብ አሳውቀዋል፤ ወደፊትም በሰፊውና በዝርዝር የሚቀጥል ነው፤ በአንድነት ውስጥ እየተካሄደ ያለው ትግል ከባድና መራራ እንደሚሆን ብዙዎች ገና አልገባቸውም፤ የአንድነትን የነቀዘ አመራር የሚያታልለው አንድ ከብዙ አቅጣጫዎች የሚሰነዘር ትችት ነው፤ ፓርቲው የራሱን የውስጥ ችግር እዚያው አድበስብሶና ሸፋፍኖ መፍትሔ በመፈለግ ፋንታ ለወያኔ መሳቂያና መሳለቂያ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚጎዳ ነው ይባላል፤ ለነዚህ ሰዎች የኢትዮጵያ ፖሊቲካ ዓላማውም ዘዴውም በጣም የተለየ ነው፤ ዓላማቸው ቁጭት መወጣት ወይም መበቀል ነው፤ ዘዴያቸው ወያኔ የሚከፋበትን መንገድ መከተል ብቻ ነው፤ ወያኔ ሲስቅ እንባቸው ይመጣል፤ ራሳቸውን በመስታወት ማየት ቢችሉ የሚያዩት ወያኔን ነበር! የአንድነት ዓላማ ይህ አይደለም፤ አንድነት ወያኔ ሳቀ ብሎ አያለቅስም፤ ዓላማውም ወያኔን ማስከፋት አይደለም፤ ዓላማውና ዘዴው ተደጋግሞ እንደተነገረው የኢትዮጵያን ሕዝብ በሰላማዊ የፖሊቲካ ትግል የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ነው፤ እንበለ ፀብ፣ እንበለ ቂም፣ በሕጋዊ ሥርዓትና በመተማመን የፖሊቲካ ትግልን የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህል ለማድረግ ነው።

ደግሞስ በወያኔ ላይ ጥፋት የምንለው ሁሉ ---- ንቅዘት፣ የሕዝብን ሀብት እንደግል አድርጎ መጠቀም፣ ለራስ ሲቀርሱ አያሳንሱ በሚል መመሪያ ሎሌዎችን እየመለመሉ ጥፋትን መካብ፣ የአደራ ሥልጣንን ገደብ አለማወቅ፣ ---- ለአንድነት ባለሥልጣኖች ሲሆን ዓይናችንን እንጨፍን፣ አእምሮአችንን እናደንዝዝ ማለት ከምን ዓይነት እምነትና ከምን ዓይነት የፖሊቲካ አስተሳሰብ የመነጨ ነው? የነቃፊዎቻችን ጭንቀት ለአንድነት ፓርቲ ነው? ወይስ በአመራር ላይ ሀነው ለራሳቸውና ለሎሌዎቻቸው በሺህ ብር የሚቆጠር ደመወዝ ደልድለው ለሚጫወቱት ነው? ወይስ ለኢትዮጵያ የፖሊቲካ ትግል አለመሳካት ተቆርቁረው ነው? ወይስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዝነው ነው? ወይስ ሌላ የሚጋልባቸው ኃይል አለ? እስካሁን ድረስ የውስጥ ትግሉን አደባባይ አወጣችሁት ከማለት ሌላ በዝርዝር በአወጣናቸው የአመራሩ ጥፋት ላይ አንድም ሰው ስሕተታችሁ ይህ ነው ያለን የለም፤ አንዳንድ አባሎች እንሽምግል ብለው መጡ፤ እኛ በደስታ ተቀበለን አበረታታናቸው፤ የነቀዘው አመራር አላዳምጣችሁም አላቸው፤ በፓርቲው ግቢ የአባላት ስብሰባ ይጠራና ጋዜጠኞችና ሌሎች ታዛቢዎች ባሉበት በግልጽ እንወያይ አልን፤ የነቀዘው አመራር አይደረግም አለ፤ እንግዲህ ከወያኔ/ኢሕአዴግ የተለየሁ ፖሊቲከኛ ነኝ ብሎና ሕዝብን ፈርቶ እንዴት ይቻላል! ምርጫው ላይ ድምፅ የሚሰጠው ሕዝብ መሆኑን ረስተውት ይሆን? ለምረጡኝ ልመና ብቻ ነው ሕዝብን ፊት ለፊት ማየት የሚገደዱት?

የምርጫው ጉዳይ ወደሦስተኛው የአንድነት ፓርቲ ችግር ያመጣናል፤ የአንድነት ፓርቲ የምርጫ ዓላማ ምንድን ነው? የአንድነት ፓርቲ ዓላማ በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዳር እስከዳር አነቃቅቶ፣ መብቱንና ግዴታውን አስጨብጦ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአንድነት ፓርቲ ቃል ኪዳን የገባበትን የኢትዮጵያን ሕዝብ በነጻነትና በእኩልነት የሚያስተናግድበት ፍትሐዊ፣ ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን ለማድረግ ነው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአገሩ የሥልጣን ባለቤት መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩ ባለቤት መሆኑን አውቆና አምኖ ለልማቱና ለእድገቱ ሙሉ ኃላፊነትን ተቀብሎና በራሱ ተማምኖ በአዲስ የተስፋና የሥራ መንፈስ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ ነው፤ ሀሳቡን በአጽንኦት ለመድገም -- የአንድነት ፓርቲ ዓላማ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንጂ የግለሰቦችን የሥልጣን ጥም ለማርካት ማመቻቸት አይደለም፤ በሌላ አነጋገር ዓላማው ምንጊዜም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ሆኖ የአንድነት ፓርቲ ፖሊቲከኞች ለዚህ ዓላማ መሳካት መሣሪያዎች እንዲሆኑ ነው።

በተጨባጭ በቅንጅት ጀምሮ አሁንም በአንድነት ውስጥ እየታየ ያለው የአንድነት ዓላማ በተገላቢጦሽ ነው፤ ፖሊቲከኞች ራሳቸውን ወደዋና ዓላማነት ለውጠው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለነሱ የሥልጣን ጥም መወጣጫ መሣሪያ ማድረግ ነው፤ እንዲህ አስተካክለን ስናየው ምርጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ነው? ወይስ ለፖሊቲከኞቹ ደመወዝና ቤት የሚያስገኝ ሥራ ለመስጠት ነው? በ1997 ምርጫ እንዳየነው ደመወዝና ቤት የፈለጉት ወደፓርላማ ተሰማሩ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ አይጠቅምም ያሉት ፓርላማ አንገባም ብለው ፍዳቸውን ተቀበሉ፤ በአሁኑ ጊዜ የአንድነት ፓርቲ የሚዘጋጀው ለየትኛው ዓላማ ነው? በተጨማሪም የአንድነት ፓርቲ መሪ፣ ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ከሕግ ውጭ በሆነ እስር ላይ ነች፤ የአንድነት ፓርቲ ወይዘሮ ብርቱካንን በእስር ቤት አስቀምጦ ምርጫ ውስጥ የሚገባው የማንን ዓላማ ለማሳካት ነው? የኢትዮጵያ ሕዝብን ዓላማ አንድ ስንዝር እንደማያራምድ ሳይታለም የተፈታ ነው፤ በጣም የሚደንቀው ነገር በአንድነት ውሰጥ ደንቦች እንዲከበሩና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲኖር በማለት ዝምአንልም በማለት የተነሣነውን አባሎች ኢሕአዴግን እያስፈነጠዛችሁ ነው ብለው የሚወቅሱን ሰዎች መሪዋ በእስር ቤት እንዳለች ወደምርጫ

መግባት ወያኔን ማስፈንጠዙን አለመናገራቸው ነው፤ ለማናቸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሱ ጥቅም የቆሙለትንና ለራሳቸው ጥቅም የቆሙትን በደንብ መለየት ይችላል።

ችግሮቹ ከባድ ናቸው፤ ከባድ የሆኑት መፍትሔ የማይገኝላቸው ሆነው አይደለም፤ የነቀዘው አመራር ለውይይትና ለክርክር በሩን ሁሉ በመዝጋቱ ነው፤ መዋቅራዊ አሠራር በሚል መጋረጃ ውስጥ ሆነው በገንዘብ ሎሌ እየገዙ፣ ለእንጀራቸው ኅሊናቸውንና ቃል ኪዳናቸውን በዘነጉና ነጻነት በሌላቸው ሰዎች የድምፅ ብልጫ የሥራ አስፈጻሚውንና ምክር ቤቱን ይጋልባሉ፤ በአለፈው ቅዳሜ በተካሄደው የብሔራዊ ምክር ቤት በተባለው ስብሰባ ላይ ለውሳኔ በቀረበው ሀሳብ ላይ የተለየ አስተያየት የሰጡ ሰዎችን ‹‹ገና ርዝራዦች አሉ›› በማለት ሊያሸማቅቁአቸው መሞከራቸውን ሰምቻለሁ፤ ይህ ጤናማ አይደለም፤ በራሳቸው የሚተማመኑና በሠሩት ሥራ የማያፍሩ ከሆነ አባላትና ጋዜጠኞች፣ ሌሎች ጥቂት ታዛቢዎችም ባሉበት ውይይት መደረጉን ለምን ይፈሩታል; እኛ ጥፋተኞችና ሐሰተኞች ሆነን ከተገኘን በአደባባይ እኛን ፊት ለፊት ለማጋለጥ ለምን ይፈራሉ; የእውነትን ብርሃን በመጋረጃ ተከላክለው አይዘልቁትም፤ መጋረጃው የሚቀደድበት ቀን እንደሚመጣ ጥርጥር የለኝም።